February 9, 2014

# ልብን የሚለውጥ ቃል

የሰው ልብ የሰው ሁለንተናው ወይም ማንነቱ ነው፡፡ልባችን ላይ የሚገኘው ማዘገብ ማንነታችን ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖን ያመጣል፡፡ከወስጣችን አዘወትሮ የሚወጣወም ነገር ማለጫችን ይሆናል፡፡በልባችን ላይ የሚዘራው ነገርና ጊዜ የምናጠፋለት ነገር ውጫዊ ድርጊታችንን በሚገባ ይወስነዋል፡፡ልባችን እና አንደበታችንም በተግባር ደረጃ የተገናኙ ናቸው፡፡አዘወትረን የምንተነፍሰው ወይም የምንናገረው ልባችንን በዋናነት የያዘወን ነገር ነው ምሳሌ 16፡23 ላይ <<የጠቢብ ልብ አፉን ያስተምራል>>ይላልና፡፡

ልባችን ላይ ያለማቋረጥ የሚዘራው ዘር(ምንም አይነት ይሁን) ወስጣችንን እየለወጠው ስለሚመጣ የቃላት አሜራረጣችንን አስተሳሰባችንንና ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነታችንን በእጅጉ ይቀይረዋል፡፡ስለዚህ በውጫዊ ነገሮች ላይ በሀይል ከሚጨነቅ ይልቅ በልባችን ላይ ለምንዘራው ዘር ልንጠቀቅ ይገባል፡፡ለዚህ ነው ምሳሌ 4፡23 ላይ <<አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የህይወት መውጫ ከእርሱ ነውና>>የሚለን፡፡አጥብቀን ልባችንን የምንጠብቅበት ዋነኛ መንገድም በልባችን ላይ የእግዚአብሔርን ቃል በማዘራት፣በማጥናት እና በማሰላሰል ነው፡፡ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሀሳብ ያለው ዘዳ 11፡18 ሲሆን ቃሉ ጠንከር ያለ ጥረትን እንደሚጠይቅም ያሳየናል፡፡ቃሉ እንዲህ ይነበባል፡-

<<እንግዲህ እነዚህን ቃሎች በልባችሁና በነፍሳችሁ አኑሩ፤እነርሱንም ለምልክት በእጃችሁ ላይ እሰሩአቸው፤በዓይኖቻችሁም መካከል እንደ ክታብ ይሁኑ፡፡>>

ቃሉን በነፍሳችን ወስጥ እንዲኖር የምናደርግባቸው መንገዶች ሁለት ናቸው፡፡የመጀመሪያው መንገድ ቃሉን ያለማቋረጥ ማጥናትና ማሰላሰል ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ቃሉን በተግባር በኑሮአችን ማለማመድ ነው፡፡እነዚህን ሁለት ነገሮች ሳናቋርጥ ስናደርግ ህይወትን የሚለወጠው ቃል በሚደረሳን ሁኔታ በልባችን ላይ ይታተማል፡፡

ዘዳግም ላይ ካለው ቃል ጋር የሚመሳሰል ቃል መዝ 119፡11 ላይ እናገኛለን፡፡ይህም ቃል እንዲህ ይላል፡-

<<አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ>>

አዎ እርሱን ላለማበደል ባለቀ ሰአት መሯሯጥ ሳይሆን አስቀድሞ ቃሉን በልብ ማሰወር ነው፡፡<<ማሰወር>>የሚለው ቃል በወስጣችን ትርጉም አግኝቶ የተዋሀደን፣የገባንን፣የራሳችን ያደረግነውን ቃል ወይም ሬማ የሆነልንን ቃል ያማከታል፡፡በጥሩ ሁኔታ ያጠናነውንና ጊዜ ሰጥተን ያሰላሰልነውን ቃል ብቻ ነው በወስጣችን ማሰወር የምንችለው፡፡ቃሉን የምንሰወረውም ገና ቃሉን ሳናስተወል ባለበት ሁኔታ ላይ ሆነን ሳለን ከአእምሮአችን ላይ የሚጥቅ ሌባ ስላለ ነው፡፡በአእምሮአችን ያላስተዋልነው ቃልም ወደ ልባችን አይገባም፤በሩ አእምሮአችን ነውና፡፡እንዲህ በወስጣችን የተሰወሩ ቃሎች በልባችን ሲበዙልን ጌታን የምናሳዝንበት እና የምንበድልበት ማጠን እያነሰ እና እርሱ በህይወታችን እየከበረ ይመጣል፡፡በሌላ አገላለጽ እየተለየን እየተለወጥንና እርሱን እየመሰልን እንሄዳለን ማለት ነው፡፡

መጽሀፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ልባችን ላይ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ይናገራል፡፡ኤር 17፡9 ላይ <<የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?>>በማለት የልባችንን ማንነት በሚገርም ሁኔታ ይነግረናል፡፡የሚገርም ነው፡፡የልባችንን የከፋት ማጠንና ስፋት እግዚአብሔር እንጂ እኛ በፍጹም አናውቀውም፡፡ከዚህም የተነሳ ነው በእራሳችን ላይ ምንም መተማመን የሌለብን፡፡ይህ ቃል ምን ያህል የጌታ ረድኤት እና ጥበብ በህይወታችን እንደሚያስፈልግን ያሳያል፡፡ስለዚህ ቃል በእንግሊዝኛ መጽሀፍ ቅዱሶች ላይ ጠንከር ያሉ ሀሳቦችን አይቻለሁ፡፡እንዲህ እተነትነዋለሁ፡፡ልባችን፡ –

- Deceitful of all things:-እጅግ አሳች/አደገኛ አሳሳች(መዝ 95፡10 ያንቡ)
- Desperately wicked :-ለከፋት የሚመለስ/ለከፋት የተሰጠ

አዎ የሰውን ልብ ማንም አያውቀውም፡፡ይህንን ለከፋት የተሰጠ ማንነት ማለወጥ የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው፡፡ሌሎች ምንጮች ታይታዊ ወይም ውጫዊ እንጂ ዘለቄታዊ ለውጥን በፍጹም አይሰጡንም፡፡ስለዚህ ነው እራሳችንን እንደ ህሙተኛ አይተንና አምነን ወደዚህ የመድሀኒቶች ሁሉ ምንጭ መምጣት የሚገባን፡፡በማርቆስ 7፡21-23 እንደምናየው ከሰው ልብ ብዙ የሚያረክስ እና ብዙ ግንኙነታዊ እና ማህበራዊ ቀውስ የሚያመጡ ነገሮች ይወጣሉ፡፡ስንዘረዝራቸው፡ –

<<ክፉ ሀሳብ፣ዝሙት፣ማረቅ፣መግደል፣ምንዝርነት፣መጎምጀት፣ክፋት፣ተንኮል፣መዳራት፣ምቀኝነት፣ስድብ፣ትዕቢትና ስንፍና>>

እነዚህ ሁሉ ከልባችን ይወጣሉ፡፡እጅግ አስፈሪ ነው፡፡ለዚህ ነው ከላይ ኤር 17 ላይ በተጠቀሰው ቃል ላይ <<የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?>>በማለት የሚናገረው፡፡<<ክፉ ሀሳብ>> የሚለው ቃል በተለይ ሰፋ ያለ ሀሳብ የያዘ ቃል ሲሆን ብዙ ክፉ ነገሮችን የማሰብ ዝንባሌዎች እንዳለን ይጠቁመናል፡፡ለዚህ ነው ሀዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፡24 ላይ <<እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ፤ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? ብሎ ጠይቆ በሚቀጥለው ማስመር ቁጥር 25 ላይ መፍትሄውን ያስቀምጣል፤እንዲህ በማለት<<በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን>>አዎ መፍትሄው አንድ ነገር ብቻ ነው <<የህይወት መንፈስ ህግ>>(ሮሜ 8፡2)!!

አዎ የእግዚአብሔር መንፈስ ካልረዳን በስተቀር ከዚህ አሳዛኝ የልብ ክፉ ዝንባሌ ማምለጥ አንችልም፡፡አንድ ነገር ብቻ ነው ማድረግ ያለብን፡፡ሊለውጠን ሀይሉ፣አቅሙ፣ብቃቱና ጥበቡ ላለው ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ እራሳችንን ማስጠት ነው፡፡ኤፌ 3፡20 ላይ<<በእኛ እንደሚሰራው ሀይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ አብልጦ ሊያደርግ ለሚችለው >> እንደሚል ለአሰራሩ መመቸትና ለምሪቱ እሺ ማለት ነው የሚያዋጣን፡፡ያኔ በውስጣችን አስደናቂ የማለወጥን ስራ ይሰራል፡፡ከዚያም ቀድሞ ያቃቱንን ነገሮች <<በእርሱ>> እየቻልናቸው በመገረምና በሀሴት እንሞላለን፡፡ክርስትናን ከሌሎች ሀይማኖቶችም ልዩ የሚያደርገውም ይሄ ነው፡፡

የልባችንን ምንነት በመንፈስ ሞት ልናደርገው የሚገባንን ጥንቃቄ እና የምንወስዳቸውን እርምጃዎች በሚገባ ይወስኑታል፡፡ዮሀ 8፡31 ያመኑትን አይሁዶች ኢየሱስ እንዲህ ነው ያላቸው፡ –

<<እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም ታውቃላችሁ እውነተም አርነት ያወጣችኋል>>

አዎ ይህ መንፈስ የሆነው ቃል ልባችን ውስጥ በተዘራውና ስፍራ ባገኘው ልክ ነጻነታችን እየጨመረ እና እየተለቀቅን እንሄዳለን፡፡በህይወታችንም ብዙ መንፈሳዊ ፍሬዎች መታየታቸው የሚቀር ይሆናል፡፡ የውስጥ ነጻነታችንና መንፈሳዊ ፍሬዎች ከቃሉ ጋር የምናደርገው የቁርኝት መጠን ውጤቶች መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል ማለቴ ነው፡፡

ልባችን ላይ ያለማስለስ የሚሠራው መንፈስ የሆነው ቃል የልባችንን አይን ስለሚያበራው መንፈሳዊውን አለምና ማንነታችን በሚገባ እያወቅን እንመጣለን፡፡ከምን አይነት ጉድም ቃሉ እያወጣን እንደሆነም በሚገባ እንረዳለን፡፡ኤፌ 1፡15-19 ይህንን ሀሳብ በግሩም ሁኔታ ይገልጸዋል፡፡እንዲህ ይነበባል፡-

<<የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡ይህም የልባችሁ አይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳን ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የሀይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው>>

ይህ ቃል እጅግ ድንቅ ሀሳብ የያዘ ቃል ነው፡<<እርሱን በማወቅ>> የሚለው ሀረግ ስለ ቀለም እውቀት አይደለም የሚናገረው፡በጸሎትና መንፈስ ከሆነው ቃል ጋር በሚኖረን ህብረት ስለምናገኘው የክርስቶስ እውቀት ነው የሚናገረው፡በእንግሊዝኛው <<relational knowledge>> ይሉታል፡፡ስለዚህ በሂደት ባስቀምጣቸው፡-

- ክርስቶስን በማወቅ(deeper relational intimacy)------->የጥበብና የመገለጥ መንፈስ-------->የልባችን አይኖች መብራት

የልባችን አይኖች ሲበሩ ምርጫዎቻችን፣የህይወት ምልልሳችን፣ድርጊታችን እና ግንኙነታችን በሚገርም ሁኔታ ይቀየራሉ፡፡ክፉ ዝንባሌዎቻችን በመልካም ነገሮች እየተዋጡ ይመጣሉ፡፡ከዚህ የተነሳ ሕይወታችን እውነተኛ ትርጉም ያገኛል፡፡ለምን እንደምኖር፤ለምን ጉዳይ ቅድሚያ ማስጠት እንዳለብን እና የትኛው ነገር ዋናው የልባችንን ክፍል ማያዝ እንዳለበት በሚገባ እንገዘባለን፡፡ከዚህም የተነሳ በኑሮአችን ስራ መፍታት እና በአልባሌ ነገሮች ጊዜን ማባከን የሚባሉ ነገር ያበቃላቸዋል፡፡በሕይወታችንም እውነተኛ እርካታን እናገኛለን፡፡ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ የሆነ የልብ ለውጥ በማምጣት የፍሬ ሰዎች እንድንሆን ለቃሉ ያልተከፋፈለ ልብን እንስጥ!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

240-330-5004

beke_abay@yahoo.com